# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
# Coalition for Unity and Democracy Party

ቁጥር
Ref.No ዐለ/3/46/2000
ቀን
Date 19/11/2000

ለ______________________

______________________

የፓርቲያችንን ስያሜ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲን የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አለአግባብ ለሌላ አካል በመስጠቱ ምርጫ ቦርድን ከሰን ከሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በፍርድ ቤት ክርክር ስናደርግ መቆየታችን ይታወቃል፡፡

ፍርድ ቤቱ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ስም መንቀሳቀስ እንደማንችል ተገልጾልናል፡፡ የፍርድ ሂደቱ ወደ ይግባኝ ተሸጋግሮ የተነፈግነውን ፍትሕ ለማግኘት ጥረት ማድረግ እንቀጥላለን፡፡ ይግባኝ የማለታችን ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ጐን ለጐን ደግሞ ስያሜያችንን አውጥተን ዝግጅት አድርገን መጠባበቅ እንዳለብን እናምናለን፡፡

ሰኔ 14 እና 15 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው የፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከተሰማ በኋላ የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴው ፓርቲያችን ትግል የሚያካሂድበትን ስትራቴጂ ነድፎ እንዲንቀሳቀስ ውክልና የተሰጠው መሆኑ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሠረት የፓርቲውን ስም ለማውጣት ተዘጋጅቷል፡፡

የፓርቲውን ስያሜ ለመምረጥ ይቻል ዘንድ በመላ አገሪቱም ሆነ በውጭ አገር የምትገኙ የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች አባላት በየደረጃው ባሉ የፓርቲው መዋቅሮች በመሰባሰብ ለፓርቲያችን ስም ሊሆን የሚችል ስያሜ በጋራ በመነጋገር ከአንድ ጀምሮ ከዚያም በላይ የስም አማራጮችን በመዘርዘር እንድትልኩልን እንጠይቃለን፡፡

አዲሱ ስያሜያችን ለምርጫ ቦርድ ተገልጾ ፈቃድ እንዲሰጠን ስንጠይቅ በፍጥነት እንዲፈጸምልን በመሻት ነው፡፡ ስለሆነም ሁላችሁም የፓርቲያችን አባላት ሳትዘገዩ 15 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የስያሜ ሃሳባችሁን እንድታሳውቁን እናሳስባለን፡፡

ፓርቲያችን በሰላማዊ ትግሉ ይቀጥላል

ከሰላምታ ጋር

ወንድወሰን ተሾመ
የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
ዋና ፀሐፊ

Tel 011-1-553506/ 011-1-551789 Fax 011-1-553155 E-mail cud.office@gamil.com
Addis Ababa–Ethiopia